የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

ነሃሴ 10 2006 ዓ.ም

# ወጣቱን በየምክንያቱ የመከፋፈል ሙከራ ይከሽፋል!

ወያኔና ጭፍሮቹ ሊታገላቸው የተነሳውን ወጣት ለመከፋፈል ያላደረጉት ሙከራ እንደሌለ የ23 ዓመት ተመክሮ አረጋግጦልናል ። የወያኔው የሚጠበቅ ሲሆን ውግዘትን ጋባዥ የሆነው ወጣቱን ከፋፋይ ሙከራ ግን ተቃዋሚ ነን ብለው የሚመጻደቁ አንዳንዶችን ይመለከታል ።

በቅርቡ አንድ በአሚሪካ ነዋሪ የሆነ ምሑር የኢትዮጵያ ወጣቶች ይሰባሰቡ በሚል ጥሪ አቅርቦ ግን ወደ ግራ ያዘነበሉትን ግን ማግለል ያስፈልጋል ብሏል ፡፡ ወክንድ ይህንን ጥሪ ሊደበቅ ያልቻለ ጸረ ወክንድነት፤ ጸረ ኢሕአፓነት ነው ሲል ይፈርጀዋል ። ትላንት ገና ያውም ወያኔ ስልጣን ይዞ ህዝብንና ሀገርን ሲበድል ከከረመ በኋላ ዓመታት ቆጥሮ ወደ ፖለቲካ መጣሁ ብሎ የተናዘዘው ግለሰብ ገና ከጠዋቱ የሚጽፈውና የሚናገረው የታጋዮችን ታሪክና አንድነት የሚጻረር፣ በተለይም የአሚሪካንን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚፍጨረጨር ሆኖ ተገኝቷል። በወጣቱ መሀል የሌለ ልዩነትን ፈጥሮ--ያውም የርዕዮተ ዓለም--አንዱን ወገን አግልሎ ማለት (የወያኔ ደጋፊዎችን ሳይሆን የወያኔ ተቃዋሚዎችን) ግቡ ለማንም ሊሰወር አይችልም፤ ማንን ለመጥቀም እንደሆነም የሚሰወር አይደለም ። ወክንድ ኢሕአፓ ለሕዝብ በመቆሙና በተለይም ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብን ለመታደግ ወጣቱን ለማደራጀት መነሳቱ ያኮራዋል እንጂ አያሳፍረውም።

ወክንድ የኢትዮጵያ ወጣቶች በርዕዮትና እምነት፤ በብሂረሰብና የፖልቲካ ዝንባሌ ሳይከፋፈሉ በጋራ ለኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና በሀገር አድን ትግሉ እንዲሰለፉ ይፈልጋል፤ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሲታገል ቆይቷል። ከፋፋዮችና የባዕድ ቅጥረኞችም ይህንን ተልዕኮውን ሊያደናቅፉ አይችሉም ብሎም ያምናል።

ከአሰመሳይ ተቃውሚዎች ጎራችን ይጽዳ !

ለሀገር አድን ትግሉ ወጣቱ በጋራ ይነሳ !!

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com